የአብርሃም ምልጃ



ሐምሌ 2006 ዓመተ ምሕረት

Scanned by CamScanner

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

የአብርሃም ምልጃ

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ከቍጥር 19 እስከ 31 ድረስ ያለውና «ቀይ ልብስና ቍጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር። አልዓዛርም የሚባል አንድ ድሀ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፥ ከባለ ጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሎቹን ይልሱ ነበር።

ድሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም አቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ። እርሱም አየጮኸ። አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ ምላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን። ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ከፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ። ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ አንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ።

እርሱም:- እንኪያስ፥ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው አለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤ እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ። አብርሃም ግን። ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው። እርሱም:- አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ፥ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ አለ። ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፥ ከሙታንም አንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው» የሚለው ታሪክ ለምልጃ ይጠቀሳል።

ይህ ታሪክ ምሳሌ ነው የሚሉ መምህራን እንዳሉ ሁሉ፤ የለም አማናዊ ታሪክ ነው የሚሉ ሊቃውንትም ሞልተዋል። ምሳሌ ነው የሚሉቱ የሚያቀርቡት ማስረጃ ከቍጥር ፲ ጀምሮ በምሳሌ ያስተምር ነበር፤ ይህም ከዚያው ጋር በተያያዘ በቍጥር 14 ላይ «ገንዘብንም የሚወዱ ፈሪሳውያን ይህን ሁሉ ሰምተው ያፌዙበት ነበር» ተብሎ ከተጻፈው ጋር በማያያዝ ነው።

ከዚህም ሌላ የአብርሃም እቅፍ በእንጻረ ሲዖል መገለጡ ተምሳሌታዊ በመሆኑ ነው የሚል ሐሳብም ያቀርባሉ።

ከዚህም ሌላ ባለጸጋው በሲዖል የሆነበት ምክንያት በምድር በደስታ ስለነበርከ ነው የሚል ሲሆን አልዓዛርም በአብርሃም እቅፍ የሆነው በከፋ ሆኔታ ላይ በመሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ሰዎች ወደ ሲዖል ሊወርዱ የሚችሉትም ሆነ ከሲዖል የሚድኑት በምድር ላይ በነበራቸው የአኗኗር ሁኔታ ነው የሚል መልእክት ያለው ይመስላል። ስለዚህ ይህ መልእክት በወቅቱ ከገንዘብ ፍቅር ጋር ለነበሩት ሰዎች የቀረበ የምሳሌ ማስተማሪያ ነው ይላሉ።

ከዚህም ሌላ አብርሃም ሙሴ እና ነቢያት አሉላቸው ያለውን ያነሳሉ። ሐሳቡንም ሲያብራሩ ሙሴ እና ነቢያት የነበሩበት ዘመን የተራራቀ በመሆኑ ሁለቱን አንድ ላይ መጥራቱ ታሪኩ በሙሴም ሆነ በነቢያት ዘመን የተፈጸመ ሳይሆን በምሳሌ የቀረበ ነው ይላሉ።

ከዚህ የተለየ ሐሳብ ያላቸው ሰዎች ግን «የለም ታሪኩ እውነተኛ ነው» ይላሉ። እነርሱ የሚያቀርቡት መከራከሪያ፤ ኢየሱስ በምሳሌ ሲያስተምር «...ምሳሌ ነገራቸው...» በሚል ነው የተጻፈው። በዚህ ስፍራ ላይ ምሳሌ እንደነገራቸው የሚያስረዳ ቃል የለም የሚል ነው።

ታሪኩ ምሳሌም ሆነ እውነተኛ አንዳንዶች ይህን ታሪክ መነሻ በማድረግ አብርሃም እንዳማለደ ያስተምራሉ። ከዚህም በመነሳት እነርሱ አለ ለሚሉት የቅዱሳን ምልጃ እንደማስረጃ አድርገው ያቀርቡታል። በርግጥ ይህ ምንባብ ለምልጃ ትምህርት ይሆን ይሆን?

በታሪኩ ላይ እንደሚነበበው ባለጸጋው መጠየቅ የሚገባውን ሦስት ጥያቄዎች ያቀርባል። እነዚህ ጥያቄዎች ምንም እንኳ ከምልጃ ጋር ባይገናኙም ጥያቄዎቹን ከመልሶቹ ጋር በማስተያየት መመልከቱ ታሪኩ ከምልጃ ጋር ምንም ትስስር እንደሌለው ለማየት ይረዳል።

የመጀመሪያው ጥያቄ «አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ ምላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ» በርግጥም በነበልባል ሥቃይ ውስጥ ላለ ሰው ከዚያ ጨርሶ መውጣት አልያም ጥቂት ጠብታ ውሃ የሚናፈቁ ነገሮች ናቸው።

ይህ በምልጃ ሰዎችን እናድናለን ከሚሉ መጻሕፍት ያነሰ ጥያቄ ነው። ከሲኦል አውጣኝ የሚል ጥያቄ አይደለምና ያቀረበው።

Scanned by CamScanner

ሰይድልኝ ለሚለው ለባለጸጋው ጥያቄ አብርሃም የመለሰው መልስ «ከዚህ ወደ አናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፣ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በአናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል» የሚል ነበር። በዚህ በአብርሃም ንግግር ውስጥ የምልጃ የተሰፋ ጭንላጭል የማይታይና ሐዝናለሁ› የሚል ነው የሚሰማው።

ይህ ምንባብ ለምልጃ ትምህርት ይሆናል የሚሉቱ ሰዎች አብርሃም ይህን ባለጸጋ «አብርሃም አባት ሆይ ማረኝ» አያለ አብርሃም ግን ምንም ያላደረገለት መሆኑን እንዴት ማስተዋል ተሳናቸው?

በቀጣይነት ባለጸጋው «አንኪያስ፣ አባት ሆይ፣ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው አለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤ እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ»

ይህ ጥያቄ ማንም ሰው፤ እርሱ በወደቀበት ውድቀት ወዳጅ ዘመዶቹ እንዳይጣድቁ የሚጠይቀው ትክክለኛ ጥያቄ ነው። ለዚህ መልካም ጥያቄ «ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው» የሚለው የአብርሃም መልስ ግን የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ መታዘዝን እንጂ ምልጃን የሚያበረታታ አይደለም።

ባለጸጋው ይህም አላስደሰተውምና «አይደለም፣ አብርሃም አባት ሆይ፣ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ» የሚል ሐሳብ ያነሳል። አውነት ነው፤ «ማን ሄዶ አየው?› ለሚል ማጉበረሰብ ሄዶ ያየውን የሚናገር ሰው ቢያገኝ ንስሐ ለመግባት የተሻለ ይሆን ነበር። ነገር ግን የአብርሃም ምላሽ «ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፣ ከሙታንም አንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው» የሚል መሆኑ ምንኛ አስገራሚ ይሆን?

አብርሃም አሁንም የሰውዬውን ሐሳብ አልተቀበለም። እንዲሁም ደግሞ በምድር ላሉት ሰዎች የቅዱሳን ምልጃ አለላቸው አልያም እኛ ላለን ምን ችግር አለው? የሚል ንግግር አላስተላለፈም። የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ብቸኛው መንገድ መሆኑን ነው አብርሃም ማሳየት የፈለገው። ታዲያ የአብርሃም ምልጃ የት ገባ?

«ኪዳነ ምሕረት» የተሰኘውና በነጻ የሚታደለው ባለ ሃያ ገጽ ጽሑፍ ደርሰዎት የማያውቅ ከሆነ
በመልእክት ሳጥን ቁጥር፡ 29783 አዲስ አበባ ወይም
በE-mail: kidmhe@gmail.com ወይም
በFace book: www.facebook.com/tewodero.demelash
ጥያቄዎንና አድራሻዎን ገልጸው ይጻፉልን።

Scanned by CamScanner